Amhara Association of America
መንቃት | መደራጀት | መታገል
Awaken, Organize, Struggle

# በኦሮሚያ ክልል በ ዐማራ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለውን ዘር ተኮር ጭፍጨፋ በተመለከተ ለአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የቀረበውን አቤቱታ በተመለከተ የቀረበ ማብራሪያ

የዐማራ ማህበር በአሜሪካ (Amhara Association of America) ከፕሪቶሪያ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ መብቶች ማእከል (Centre for Human Rights, Pretoria University) ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል በዐማራ ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን በመንግስት መዋቅር የሚደገፍ መጠነሰፊ ዘር ተኮር ጭፍጨፋና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ የኢትዮጲያ መንግስትን በመክሰስ ለአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (African Commission on Human and Peoples' Rights) አቤቱታ ማቅረቡ ይታወቃል። የቀረበውን አቤቱታ በተመለከተ ለዐማራ ህዝብ እንዲሁም ጉዳዩ ይመለከተናል ብለው ለሚያስቡ አካላት ሙሉ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ቅሬታው ስለቀረበለት የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ አፍሪካ ኮሚሽን በሚል የሚጠቀስ) ምንነትና አሰራር፣ ስለ ቅሬታው ይዘት፣ የቅሬታው ፋይዳ እንዲሁም ወደፊት መደረግ ስላለባቸው እንቅስቃሴዎች በተመለከተ የሚከተለው ማብራሪያ ቀርቧል።

## የአፍሪካ ኮሚሽን ምንነትና ቅሬታዎችን ተቀብሎ የመመርመር ስልጣን

የአፍሪካ ኮሚሽን እ.ኤ.አ በ1981 ናይሮቢ፣ ኬንያ ላይ በተካሄደው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ 2002 ጀምሮ አፍሪካ ህብረት ተብሎ በአዲስ መልክ የተቋቋመ) አሥራ ስምንተኛው የመሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ ይሁኝታ አግኝቶ በአፍሪካ ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ለማራመድና ለመጠበቅ የወጣውን የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተርን (በተለምዶ የባንጁል ቻርተር ተብሎ የሚገለጽ) አተገባበር በተመለከተ የበላይ ጠባቂነትና ተርጓሚነት ሥራን እንዲሰራ የተቋቋመ በከፊል የፍ/ቤት ባህሪ ያለው አህጉራዊ ተቋም ነው። የኮሚሽኑ መቀመጫ በጋምቢያ ዋና ከተማ ባንጁል ሲሆን በየ ስድስት አመቱ ባላቸው ስነምግባርና መልካም ስም ፣ በሰብአዊ መብቶች መስክ ባላቸው ችሎታና የህግ ልምድ የባንጁል ቻርተርን ከተቀበሉ የአፍሪካ አገሮች በሚመረጡ 11 ባለሙያዎች የተዋቀረ ተቋም ነው። የባንጁል ቻርተርን የተቀበሉ አባል ሀገሮች (ኢትዮጲያን ጨምሮ) በቻርተሩ ተቀባይነት ያገኙትን መብቶችና ነጻነቶችን በአግባቡ ይተገበሩ ዘንድ የአፍሪካ ኮሚሽን የመቆጣጠርና የመከታተል ስልጣን ያለው ሲሆን ይህም ስለ መብቶቹና ነጻነቶቹ ግንዛቤ የማስፋፋት፣ የማስጠበቅና የማስከበር ሀላፊነቶችን ይጨምራል። በቻርተሩ ላይ እውቅና የተሰጣቸውን መብቶችና ነጻነቶች የማስጠበቅና የማስከበር ሀላፊነቱን ለመወጣት ለ ኮሚሽኑ ከተሰጡት ስልጣኖች መካከል በአባል ሀገራት ላይ የሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ በግለሰቦች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን (individual complaints) የመቀበል፣ የመመርመርና የውሳኔ ሀሳብ የመስጠት ስልጣኑ ይገኝበታል። ይህንን የቅሬታ አቀራረብ ስርአት በመጠቀም በባንጁል ቻርተር እውቅና የተሰጣቸው መብቶች ጥሰት ሰለባ የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ወይም እነሱን በመወከል ለሰብአዊ መብቶች መከበር የቆሙ ግለሰቦችና ድርጅቶች በአባል ሀገራት ላይ ክስ ማቅረብ ይችላሉ። የዐማራ ማህበር በአሜሪካም ይህንን የቅሬታ አቀራረብ ስርአት መሰረት በማድረግ ከፕሪቶሪያ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ መብቶች ማእከል ጋር በጋራ በመሆን የኢትዮጲያ መንግስት በኦሮሚያ ክልል በዐማራ ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን መጠነሰፊ ዘር ተኮር ጭፍጨፋና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን

ባለማስቆሙና በባንጁል ቻርተር እውቅና ያገኙ መብቶች ና ነጻነቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታውን ባለመወጣቱ ተጠያቂነት አለበት ሲል ለኮሚሽኑ ቅሬታውን አስገብቷል።

## የ ቅሬታው ይዘት

የዐማራ ማህበር በአሜሪካ ከፕሪቶሪያ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ መብቶች ማእከል ጋር በመተባበር ያቀረበው ቅሬታ በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉድሮ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ እና ምእራብ ሸዋ ዞኖች በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ሀይሎች አማካኝነት ባለፉት ሁለት አመታት ( እ.ኤ.አ 2021 እና 2022) ለጅምላ ጭፍጨፋና መጠነሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እየተጋለጡ ያሉ የዐማራ ብሄር ተወላጆችን የሚመለከት ሲሆን በቀረበው ቅሬታ ላይ የሚከተሉት ነጥቦች ተነስተዋል።

- የዐማራ ህዝብ እ.ኤ.አ ከ1991 ጀምሮ ዐማራነትን በጠላትነት ፈርጀው በተነሱት በትህነግ (በትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር) እና በኦነግ (በኦሮሞ ነጻነት ግንባር) አማካኝነት በተጫነበት ዐማራ ጠል የጎሳ ፌደራሊዝም (አፓርታይድ ስርአት) እንዲሁም በመንግስትና ከመንግስት ውጪ ባሉ ፖለቲከኞች በተዘራ ዐማራ ጠል ትርክቶች ሳቢያ መጠነ ሰፊ ጭፍጨፋዎች፣ ጅምላ ማፈናቀሎች፣ ማሳደዶች እንዲሁም ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሰለባዎች እንደነበረ፤
- በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በብዘት ተበትኖ የሚገኘው የዐማራ ህዝብ ተወልዶ ባደገባቸው ቦታዎች ሳይቀር እንደ መጤ ተቆጥሮ የተለያዩ መብቶቹ (የፖለቲካ ተሳትፎ የማድረግ መብቱን ጨምሮ) በማንነቱ ብቻ ሲነፈጉ መቆየታቸውን፤
- ከእ.ኤ.አ ከ2018 ጀምሮ በጠ/ሚር አብይ አህመድ የሚመራው ኦሮሞ መር ቡድን የስልጣን መንበሩን መቆጣጠሩን ተከትሎ በዐማራው ላይ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም በኦሮሚያና በቤንሻንጉል ክልሎች የሚደርሰው ጭፍጨፋ ከመቼውም ጊዜ በመጠንም ሆነ በጭካኔ ደረጃ የጨመረ መሆኑን፤
- በዋነኛነት በኦሮሚያ ክልል ንጹሀን የዐማራ ብሄር ተወላጆች ማለትም ህጻናት፣ ነፍሰጡሮች፣ አካልጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ህሙማኖች በማንነታቸው ብቻ እለት በእለት በኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ ሸኔ) ታጣቂዎችና በተባባሪዎቻቸው እንዲሁም በመንግስት የጸጥታ አካላት (የኦሮሞ ልዩ ሀይል አባላትን ጨምሮ) ጭካኔ በተሞላበት መልኩ እየተጨፈጨፉ እንደሆነ፤
- በኦሮሚያ ክልል የሚደርሱ ዘር ተኮር ጭፍጨፋዎችን በሚያጋልጡና በሚያወግዙ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ጋዜጠኞችና ማህበራዊ አንቂዎች ላይ እዲሁም ተቃውሞአቸውን በ ሰልፍና በሌሎች ሰላማዊ መንገዶች ለመግለጽ በሚሞክሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ የመንግስት ሀይሎች አፈና፣ እስር፣ ግድያና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን እየፈጸሙ እንደሚገኝ፤
- ዘር ተኮር ጭፍጨፋዎች በሚፈጸሙበት ጊዜና ከተፈጸሙ በኋላ መረጃዎች እንዳይወጡ ለማድረግ በመንግስት በኩል የግንኙነት አገልግሎቶች (የስልክና የበይነ መረብ አገልግሎቶች) እንዲቋረጡ መደረጋቸውን፤

እነኝህና ሌሎች ኢ-ሰብአዊ የሆኑ ድርጊቶች ሲፈጸሙ መንግስት በድርጊቶቹም ሆነ ባሳየው ዳተኝነት ሳቢያ በአፍሪካ የሰዎችና ህዝቦች ቻርተር እውቅና የተሰጣቸውን መብቶችና ነጻነቶች ከማክበርና ከማስከበር አንጻር የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ በመቅረቱ ተጠያቂነት እንዳለበት በቀረበው አቤቱታ ላይ ተመልክቷል። ይሄውም መንግስት በተለያዩ መንግስታዊ ተቋማቶቹ/አካላት በተለይም በኦሮሞ ልዩ ሀይል እየተፈጸሙ ላሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በተለይም ግድያዎች፣ ህገወጥ እስሮች፣ የንብረት ውድመቶች፣ የመገናኛ ዘዴዎች መቋረጦች፣ ሰልፈኞችን በሀይል መበተን እንዲሁም ማፈናቀሎች ተጠያቂነት እንዳለበት ተጠቅሷል። ከዚህ ባሻገር የኦሮሞ ነጻነት ግንባር እንዲሁም ጋሻግሬዎቹ እየፈጸሙት ያሉትን አረመኔያዊ ጭፍጨፋዎችና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማስቆም መንግስት በቂ እርምጃ ባለመውሰዱ፣ በዚህ እኩይ ድርጊት የተሳተፉ አካላትን ለህግ እንዲቀርቡ ባለማድረጉ

እንዲሁም በሀገሪቱ በ ተለይም በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ዜጎች መብቶቻቸው ተከብሮ እንዲኖሩ የማድረግ ግዴታውን ባለመወጣቱ እና በዚህም ሳቢያ የዐማራ ብሄር ተወላጆች በማንነታቸው ብቻ በአፍሪካ የሰዎችና ህዝቦች መብቶች ቻርተር የተደነገጉ መብቶቻቸውን እንዲያጡ መደረጉን በአቤቱታው ተመልክቷል። እነዚህ የተጠቀሱት በቀጥታ በመንግስት ሀይሎች የተፈጸሙ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች እና መንግስት ባሳየው እንዝህላልነት ወይም ተባባሪነት ሳቢያ በኦሮሞ ነጻነት ግንባርና በጀሌዎቹ አማካኝነት የተፈጸሙ ጭፍጨፋዎችና ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች የባንጁል ቻርተር በመንግስት ላይ የሚጥላቸውን ግዴታዎች እንደሚጥሱ በአንክሮ ተመልክቷል። በተለይም የሚከተሉት የባንጁል ቻርተር ድንጋጌዎች እንደተጣሱ በቀረበው አቤቱታ ላይ በዝርዝር ለማሳየት ተሞክሯል።

- አንቀጽ 1(በቻርተሩ ላይ የተቀመጡ መብቶችና ነጻነቶችን እውቅና መስጠትና እንዲተገበሩ የማድረግ ግዴታ)፤
- አንቀጽ 2 እና 3 (በቻርተሩ እውቅና ያገኙ መብቶችና ነጻነቶችን ያለምንም መድሎ የመጎናጸፍና በህግ ፊት በእኩል የመታየት መብቶች)፤
- አንቀጽ 4 እና 5 (በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት፣ ጭካኔ ከተሞላበት አያያዝ የመጠበቅ መብቶች)፤
- አንቀጽ 6 እና 7 (ያላግባብ ነጻነትን ያለማጣት እና ፍትህ የማግኘት መብቶች)፤
- አንቀጽ 9 ና 11 (ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ መረጃ የማግኘት ና የመሰብሰብ መብቶች)፤
- አንቀጽ 12 (የመንቀሳቀስ ነጻነት)፤
- አንቀጽ 13 (የፖለቲካ ተሳትፎ የማድረግ መብት)፤
- አንቀጽ 14 (የንብረት መብት)፤
- አንቀጽ 16፣ 17 እና 19 (የመማር፣ የጤና፣ የ ህዝቦች እኩልነት እና የመብቶች ተጠቃሚነት)

## ከኮሚሽኑ የተጠየቁ ዳኝነቶች

ከላይ የቀረቡትን የአቤቱታ ነጥቦችን መርምሮ ከዚህ በታች የተጠየቁትን ውሳኔዎችን እንዲሰጥ ና መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን በተመለከተ አቅጣጫዎችን እንዲያስቀምጥ ለአፍሪካ ኮሚሽን በቀረበው አቤቱታ ላይ ዳኝነት ተጠይቋል።

- በኮሚሽኑ የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ በዐማራ ተወላጆች ላይ እየደረሰ የሚገኘውን ዘር ተኮር ጭፍጨፋ ለማስቆም የኢትዮጲያ መንግስት አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወስድ፤

- የኢትዮጲያ መንግስት በአማራ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ላለው ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሀላፊነት እንዳለበትና በዚህም ምክንያት በባንጁል ቻርተር የተጣለበትን ግዴታዎች በተለይም አንቀጽ 1, 2, 3, 4, 5, 6, 7, 9, 11, 12, 13, 14, 16, 17, 19 እና 25 እንዳልተወጣ/ እንደጣሰ ውሳኔ እንዲሰጥ፤
- የኢትዮጲያ መንግስት በዐማራ ተወላጆች በተለይም በኦሮሚያ በሚኖሩ ዐማራዎች ላይ እየደረሰ ያለውን ሰብአዊ መብት ጥሰቶች በተመለከተ በጥናት የታገዘ ስትራቴጂ በመቅረጽ፣ ህግና ፖሊሲዎች በማውጣት ህጋዊ መብታቸውና ጥቅማቸው እንዲጠበቅ፣ የሚደርስባቸው ዘር ተኮር ጥቃቶች እንዲቆሙ እንዲሁም ህይወታቸው፣ ክብራቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ እንዲያደርግ ፤
- የኢትዮጲያ መንግስት በተፈጸመባቸው ዘር ተኮር ጥቃት ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዐማራ ተወላጆችን መልሶ እንዲያቋቁምና እንዲደግፍ እንዲሁም በጥቃቱ ሳቢያ የተጎዱ አካል ጉዳተኞችን፣ አሳዳጊ ያጡ ልጆችን፣ አዛውንቶችንና ሌሎች ለጉዳት የተጋለጡ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚደግፍ ፕሮጀክት እንዲቀርጽ፤
- የኢትዮጲያ መንግስት በዐማራ ተወላጆች ላይ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙና ያስፈጸሙ አካላት ላይ ትጋት በተሞላበትና ግልጸኝነት ባለው መልኩ ምርመራ እንዲያደርግ እንዲሁም ክስ እንዲመሰርት፤
- የኢትዮጲያ መንግስት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገመንግስት፣ የኦሮሚያ ህገመንግስት እና ሌሎች ማግለልና መድሎ የሚንጸባረቅባቸው ህጎችን እንዲሻሻሉ እንዲያደርግ እና በሀገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ ዜጎች በማንነታቸው መድሎ ሳይደረግባቸው የሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ እንዲያመቻች፤
- የተፈጸሙትን ዘር ተኮር ጥቃቶች በተመለከተ መንግስታዊ እውቅና በይፋ እንዲሰጥ፣ ለተጠቂዎችና ለቤተሰቦቻቸው በይፋ ይቅርታ እንዲጠየቅ፤ ተጠቂዎች የሚታሰቡበት ፕሮግራም እንዲዘጋጅ እንዲሁም በኮሚሽኑ የሚሰጠውን ውሳኔና የሚቀርበውን ምክረሀሳብ በጠቅላላ አልያም በከፊል በሀገሪቱ ጋዜጣ ላይ እንዲታወጅ ወይም ሌሎች ኮሚሽኑ ያመነባቸውን ርምጃዎች የኢትዮጲያ መንግስት እንዲወስድ፤

  እነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ኮሚሽኑ ምርመራ አድርጎ ዳኝነት እንዲሰጥ የዐማራ ማህበር በአሜሪካ ከፕሪቶሪያ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ መብቶች ማእከል ጋር በመተባበር ባቀረበው አቤቱታ ላይ ጠይቋል።

## የቀረበው አቤቱታን በተመለከተ ቀጣይ የሚኖሩ ሂደቶች

የቀረበው አቤቱታ በ አራት ዋና ዋና የኮሚሽኑ የአቤቱታ ምርመራ ሂደቶች የሚያልፍ ይሆናል። እነኝህም seizure; admissibility; merits and remedies በሚል ይታወቃሉ።

**Seizure** stage የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን በዚህ ወቅት ጋምቢያ የሚገኘው የኮሚሽኑ ሴክሬታሪአት ጽ/ቤት/ኮሚሽኑ የቀረበውን አቤቱታ በማየት ብቻ ሊሟሉ የሚገባቸውን ፍሬነገሮችን/መረጃዎችን መያዝ/አለመያዙን እንዲሁም በቻርተሩ ላይ የተቀመጡ መብቶችና ነጻነቶች ተጥሰው ይሆናል ብሎ ለማሰብ አመላካች ሁኔታዎች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን ይመረምራል። ይህን ተከትሎ ጽ/ቤቱ የቀረበው ቅሬታ የተሟላ መሆኑንና ፍሬነገሮቹ በማስረጃ ከተረጋገጡ በቻርተሩ ላይ የተቀመጡ መብቶችን ጥሰት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ፍንጭ የሚሰጡ ሆኖ ካገኛቸው ቅሬታውን እንደሚይዘው መወሰኑን ለቅሬታ አቅራቢዎችና ለኢትዮጲያ መንግስት ያሳውቃል። ይህ ሂደት ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ እንደሚኖርበት የኮሚሽኑ Rules of Procedure በአንቀጽ 115(8) ላይ ያስቀምጣል።

Admissibility and merits stages: ኮሚሽኑ/የኮሚሽኑ ሴክሬታሪያት ቅሬታውን እንደሚይዘው ከወሰነ በኋላ ለቅሬታ አቅራቢዎች ያቀረቡት ቅሬታ በፍሬነገር ደረጃ ከመመርመሩ በፊት ተቀባይነት እንዲያገኝ ማሟላት ያለበትን ቅድመሁኔታዎች (admissibility criteria) ያሟላ መሆኑን እንዲሁም በአቤቱታው ላይ የተገለጹትን የስረነገር ጉዳዮችን (merit issues) የሚደግፉ መከራከሪያ ሀሳቦችንና ማስረጃዎችን በ60 ቀናት እንዲያቀርቡ ያደርጋል። ቅሬታ አቅራቢዎች በ ቅድመ ምርመራና በስረነገር ጉዳዮች ላይ መከራከሪያቸውንና ማስረጃዎቻቸውን ካቀረቡ በኋላ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ የቀረበውን አቤቱታና በቅሬታ አቅራቢዎች የቀረቡ መከራከሪያዎችንና ማስረጃዎችን ለኢትዮጲያ መንግስት በመላክ ምላሹን በ60 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ይጠይቃል። በመቀጠል ከመንግስት በኩል የሚሰጠውን ምላሽ ኮሚሽኑ በ14 ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢዎች እንዲደርሳቸው በማድረግ የመልስ መልስ ካላቸው በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርቡ እና ይህንንም ለመንግስት እንዲደርሰው ያደርጋል። ከዚህ ባሻገር ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለተከራካሪዎች በተገደበ ጊዜ ውስጥ ደጋፊ ሀሳቦችን በጽሁፍ እንዲያስገቡ እድል ሊሰጥ ይችላል፤ እንዲሁም ለምርመራው ይረዱኛል የሚላቸውን መረጃዎች፣ ሰነዶች ወይም አስፈላጊ ነገሮችን ተከራካሪ ወገኖች እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ኮሚሽኑ በቀዳሚነት ከ admissibility ጋር የተያያዙ የቅድመ ምርመራ ጉዳዮች ላይ እልባት የሚሰጥ ሲሆን የቀረበውን አቤቱታ ተቀብሎ እንዳያይ በኢትዮጲያ መንግስት የቀረቡ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ካሉና አሳማኝ አይደሉም ብሎ ካሰበ ወይም መቃወሚያ ባይቀርብም ባለው መረጃና ማስረጃዎች ላይ ተመስርቶ ሲመለከተው ቅሬታውን በቅድመ ምርመራ ምዘና ውድቅ የሚያደርጉት ሁኔታዎች ከሌሉ አቤቱታውን ለምርመራ እንደተቀበለው ውሳኔ ይሰጣል። በመቀጠል የቅሬታውን የስረነገር ጉዳዮች በተመለከተ አስፈላጊውን ምርመራ አድርጎ በጨረሰ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ቅሬታ የቀረበበት የኢትዮጲያ መንግስት ለደረሱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሀላፊነት አለበት/የለበትም የሚለውን ይወስናል። ሀላፊነት አለበት ብሎ ከወሰነ የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ርምጃዎች በተመለከተ በቅሬታ አቅራቢዎች የተጠየቁ ዳኝነቶችን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ አቅጣጫ ያስቀምጣል። የደረሰበትንም ውሳኔ ለአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ሪፖርት የሚያደርግ ይሆናል።